## ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 36 ኛ ሳምንት

# የምስራች መላእክት

**ዓላማ፡-**

- የቅዱሳንን መላእክት ሥራ መማር

**ምንባብ፡-**

- ሉቃ.2፤10-11 ማቴ. 28፤5-6

**መግቢያ**

- መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው፡፡ ስለኛ ይፀልያሉ ፤ በብዙ መንገድ ይረዱናል፡፡
- ዛሬ ለኛ /ለሰው ልጆች በሙሉ / መልካም ዜና ያበሰሩባቸውን እንማራለን፡፡

1. **መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል** የሰው ልጆች ድኅነት ሲታወጅ የተላከ መላአክ ነው፡፡እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትጸንስና እንደምትወልደው አብስሯታል፡፡
2. በመጀመሪያ ገና ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ መላእክት እረኞችን ልደተ ክርስቶስን አብስረዋቸዋል፡፡መልአኩ እንዲህ ነበር ያላቸው፡- "***ዛሬ ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምስራች እነግራቸዋለሁ፡፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት የሚሆን ጌታ ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና አትፍሩ፡፡***"
3. በትንሳኤ ታሪክ መላእክት ምን እንደሰሩ ታስታውሳላችሁ? አዎን! መላእክት የክርስቶስን ትንሳኤ ለሴቶች አብስረዋል፡፡ ጌታ በተሰቀለበት ቀን በተቀበረበት ቦታ ኀሎኅታ ተገኝተው በዚህ ቀን መላእክቱ እንዲህ ነበር ያሉዋቸው ***"አትፍሩ እናንተስ ክርስቶስን እንድትፈልጉ አውቃለውና ከዚህ የለም ተነስቷል፡፡"***
4. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምናገኘው የባህራንን የሞት ደብዳቤ ወደ ሕይወት የተቀየረው በመላእክቱ እርዳታ ነበር፡፡ መልካም ዜና ሲያበስሩንም ከእኛ ጋር ይደሰታሉ፡፡ በገና (ጌታ ሲወለድ) ***"በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር በጎ ፈቃድ ለሰው ልጆች …"*** ሲሉ ዘምረዋል፡፡

**ልምምድ**

1. መላእክት ምን ዓይነት መልእክት ወደኛ ያመጣሉ?
2. በገና ምሽት መላእክት የዘመሩት መዝሙር ምን ነበር?
3. የጌታን መወለድ ትንሳኤን ያበሰረው ማነው?

**መዝሙር**

ሚካኤል መልአከ ምህረት (2)

በረከትህ ይደር በእኛ ሕይወት (4)

ይቆየን፡፡